# ABOUT-LAW

# Featured Blogs

December 11, 2023

## ነገሩን ፍጁት

## የውርስ ንብረትን ስለመረከብ|

በራህዋ ተስፋዬ ቸርነት፤ LL.B, LL.M, LL.M



## መግቢያ

ውድ አንባብያን፤ ከውትሮው በመጥፋቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ሰላም እንደሆናችሁ ተስፋ በማድረግ እንደወትሮው ለጉዳያችሁ መፍትሄ ለብሶታችሁ ማበሻ ይዞ የሚጠብቃችሁን ህግ ፈርታችሁ እንዳትሸሹ ትውውቅ የምትሆን ጦማር ይዤ ብቅ ብያለሁ:: መልካም ቆይታ እንዲሆንላችሁ ምኞቴ ነው::

ከህይወት ጅማሬ ጋር እጅ ለእጅ አብሮ የሚሄደው ሞት ደጃፋችንን ሳያንኳኳ ለዘለአለማችን መዝለቅ ከቻልን ወይ በጣም እድለኞች ወይም ቀድሞ ወራጆች ነን። መሀል ቤት ያለነው ግን የምናፈቅራቸው አሳዳጊዎቻችን፤ አስከታዮቻችን፤ ወላጆቻችን ቀድመውን አፈር እንደሚለብሱ እየፈራን የምንቀበለው እውነታ ነው። ይህ ክፉ ቀን ዳብሶን ያለፍን ጊዜ ደግሞ ከመለየታቸው ምሬት ጋር እኩል የምናስታውሰው በዚች ምድር ያፈሯትን ንብረት ለመቀበል ከተፍ ብሎ የሚመጣብን ግዴታ ነው። በተገቢው ይህንን ማድረግ በአንድ ጎኑ መጽናኛችን ነው። ቢወልዱን ባይወልዱንም ያበቁን አባት እናቶቻችን የተውልንን ቅርስ በትክክል መቀበል መቻሉ ኩራት ያጎናጽፋል፤ ልፋታቸው አስተዋይነትን እንደለገሰን ለኛም ለሌሎችም ያሳያል። በሌላ ጎኑ ይህን ትሩፋት መጣል፤ መስመር መጣስ የመጥፎነት መጀመሪያ፤ ጎልቶ መታያ እንደሆነም ብዙው ስለሚያምን አቤት የሚደርስብን መብጠልጠል... ይህን እንዴት እናስቀረው???

አንድ ግለሰብ ለሞቱ ሊዘጋጅ ላይዘጋጅም ይችላል። ወራሾች ግን ህጉ እኛን ለመጠበቅ ያዘጋጀው መዋቅር አለልን ይህም የውርስ ህግ ይባላል።በዚህ ዘርፍ ወራሾች፤ የሚች ሰዎች እንዴት ከንብረቱ እንደሚቋደሱ ዝርዝር መረጃ ያለ ሲሆን ጥልቅ እውቀቱን በዚህ ሂደት እጃችሁን ለሚይዙት ህግ አዋቂዎች ትተን እናንተ ማወቅ ስላለባችሁ ጥቂት እናውጋ።ከጥቂት ጊዜ በፊት ባለንብረቶች በኑዛዜዎቻቸው ወራሾቻቸውን እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ተነጋግረን ነበረ። ዛሬ በሌላ ጎኑ፤ ይህም አውራሾች ንብረት ትተው በሚሄዱ ጊዜ የወራሾች ድርሻ ምንድን ነው? ስለሚለው እንወያይ።

፩. የውርስ ንብረትን መረከብ ሶስት ዋና ዋና እርምጃዎችን ያካትታል። ወራሽነትን ማስደንገግ፤ የውርስ አጣሪዎችን መሾም እና የውርስ ማጣራት ማድረግ፤ እና ውርስን መከፋፈል። በፌደራል አስተዳደሮች እና በክልሎች በነዚህ አሰራር ልዩነት ያለ ሲሆን ይህ ምን እንደሆነ የአቅራቢያችሁን የህግ ባለሙያ ጠይቃችሁ እንድታጣሩ እጋብዛለሁ። ጉዳዩ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር ስለ ውርስ ክፍፍል በዚች ጽሁፍም አልዳስስም። በሌላ ቀን የምንመለስባት ይሆናል።

፪. በመጀመሪያ ወራሽ ነኝ የሚል ግለሰብ ይህ እውነታ በሌሎች ተቀባይ እንዲሆን ይህንን ማጸደቅየሚዘረዝረው ሂደት ወራሽነትን ማሳወጅ ይባላል። በፌደራል ፍርድ ቤቶች እንደምሳሌ እንዴት እንደሚደረግ እናውራ፡ በፌደራል አስተዳደሮች ወራሽነትን ማሳወጅ በከተማ ፍርድ ቤቶች የሚደረግ ሲሆን ሂደቱም በአፋጣኝ ስነስርዓት ነው። ወራሾች ነን ባዮች አቤቱታ፤ ቃለ መሃላ፤ መታወቂያቸውን፤ አውራሽ መሞቱን የሚያስረዳ የሞት ሰርቲፊኬት፤ ያላቸውን ግንኙነት ሊመሰክሩ ከሚችሉ ምስክሮች ስም ዝርዝር ጋር ይዘው ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። ፍርድ ቤቱም ይህንን አቤቱታመርምሮ የወራሽነት ፍርድ ከሰጠ ወራሽ እንደሆናችሁ የሰነድ ምስክር አገኛችሁ ማለት ነው።

፫. የወራሽነትን ፍርድ ያገኘ ግለሰብ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከሆነ አሁን ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት በመሄድ የውርስ ማጣራት ሂደቱን ማስጀመር ይችላል። ውርስ ማጣራት በአጭሩ

ሲብራራ ሟች ትቶት የሄደው ንብረቶች እና ሃላፊነቶች ምን እንደሆኑ እና እነዚህም በወራሾች መካከል እንዴት እንደሚሰተሩ የሚለይበት ሂደት ነው። ስለዚህ ውርስ ማጣራት የአንድን ወራሽ ድርሻ ከመለየት አንጻር መሰረታዊ የሆነ አስፈላጊነት እንዳለው ከዚህ መረዳት እንችላለን። የውርስ ፍርድ የያዙ ግለሰቦች ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት ፍርድ ቤቱ፡ 1ኛ ውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው እና 2ኛ ውርሱን ለማጣራት የሚያስፈልጋቸውን ምርመራ ለማድረግ የሚያስችላቸውን እና ሌሎች አካላት እንዲተባበሯቸው የሚገልጸውን ትዕዛዝ እንዲጽፍላቸው ነው።

፬. ውርስ ማጣራት በውርስ አጣሪ ይከናወናል። ይህ ግለሰብ ማን ነው ቢባል በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በህጉ አሰራር ውርሱን ለማጣራት የሚሾመው ግለሰብ ነው። ህጉ በመጀመሪያ ደረጃ ወራሾችን ውርስ አጣሪ አድርጎ ይሾማል። እነዚህም ግለሰቦች ውርስ በማጣራት ሂደት ውስጥ በጋራ ሃላፊነት ያለባቸው እና በሂደቱም እኩል ስልጣን ያላቸው ይሆናሉ። ሟች ውርስ አጣሪ ማን እንደሚሆን በኑዛዜ ሾሞ ማለፍ ይችላል። ወራሾች በማይታወቁበት ጊዜ፤ ውርሱን ለማጣራት ወራሾች ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ በውርስ አጣሪነቱ ጉዳይ ወራሾች እርስ በራሳቸው ካልተስማሙ፤ ወራሾች ፍርድ ቤቱን ከጠየቁ ወይም ወራሽ በሌለበት ውርሱ በመንግስት የሚወሰድ ከሆነ ደግሞ በፍርድ ቤት 3ኛ ወገን የውርስ አጣሪ የማጣራቱን ስራ ሊያከናውን ይችላል። ውርስ አጣሪ ስራውን እንዲሰራ ባይገደድም በዚህ ስራ ስር ለሚያከናውናቸው ተግባራት ህጋዊ ሃላፊነት አለበት። ክፍያ የመጠየቅም መብት አለው።

፭. ስለዚህ የውርስ አጣሪ ዋና ተግባራት ምን ናቸው? ውርስ አጣሪ ሟቹ ኑዛዜ ትቶ የሞተ እንደሆነ ይህንን ያፈላልጋል። ውርሱ ተጣርቶ እስኪያልቅ ድረስ ውርሱን ያስተዳድራል፤ እዳዎች ካሉ ይከፍላል፣ ተከፋይ የሚሆኑ ገንዘቦችን ይሰበስባል። ሟች ያስተላለፋቸውን ስጦታዎች የሚሰጥ ሲሆን በዚህ ውቅት ንብረቱ እንዳይባክንም አስፈላጊ የሚሆኑን የጥንቃቄ እርምጃዎች ይወስዳል። ከህጋዊ ኃላፊነቶቹ ባሻገር እነዚህን ስራዎች በተገቢው ስለመስራቱም ፍርድ ቤቱ ማስተማመኛ ካስፈለገው ዋስትና ይገባል። ይህ ብቻ አይደለም ወራሾችም ሆነ ፍርድ ቤቱ ስራውን ለመስራት መሄድ ያለበትን መንገድ በተመለከተ ትዕዛዝ ሊሰጡትም ይችላሉ። ነገር ግን እዚህ ላይ ሳይታለፍ መነሳት ያለበት ጉዳይ ቢኖር ውርስ አጣሪ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት አከናዋኝ እንጂ ፈራጅ እና ጉዳይ ጨራሽ እንዳልሆነ ነው። ውርስ አጣሪው ስሌቶቹን ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማድረግ ነው ዋና ተግባሩ። ይህ ንብረት ለእገሌ ይገባል ይህ የእንትና ነው ማለት አይችልም። ይህ የፍርድ ቤቱ ስራ ስለሆነ ከመስመር አንለፍ።

፮. ውርስ አጣሪ በመጀመሪያ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሟቹ ኑዛዜ ትቶ ማለፉን ነው። ኑዛዜ ከተገኘእናበህግ የሚጠበቅባቸውን ፎርማሊቲዎች ካሟላ በኋላ በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ ኑዛዜው ወራሾች እና በኑዛዜው ስጦታ የተደረገላቸው ግለሰቦች በተገኙበት እንዲነበብ ያደርጋል። ይህ ኑዛዜ በሚያስቀምጠው መሰረት የሚደርስን ድርሻ ወራሾች እንዴት

እንደሚደርሳቸው ያሰላል። ይህ ሂደት ኑዛዜውን ማጸደቅን፣ ሟች ባዘዘበት ወይም ህጉ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ኑዛዜ ማንበብ እና ተቃውሞዎች ካሉ መቀበልን ይጨምራል።

፯. ሟቹ ኑዛዜ ሳይተው ካረፈ የርስቱ መጠን ምን እንደሆነ፣ ወራሾች ማን እንደሆኑ እና ድርሻቸው ምን ምን እንደሚሆን የመለየት ሃላፊነት የውርስ አጣሪው ይሆናል። ይህንን ለማድረግወራሾቹን ጨምሮ የተለያዩ አካላት ፊት የተተው ንብረቶችን ዝርዝር መሰብሰብ፣ ባለዕዳዎች ማንነታቸው እንዲለይ እንዲቀርቡ መጥራት፣ የተደረጉ ስጦታዎች ካሉ እነሱ ለማን እንደታሰቡ እና እንዴት እንደሚሰጡ ውርስ አጣሪዎች መለየት አለባቸው። እነዚህን ሂደቶች አንድ ባንድ እንቃኝ፡

፰. አውራሹ መሬት ከነበረው ውርስ አጣሪዎች መሬቱን የሚያስተዳድረው አካል ፊት የሚያስቀርብ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማግኘት አለባቸው። የመሬት ይዞታዎችን ማስተዳደር በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በክፍለ ከተማዎች የሚደረግ ተግባር ሲሆን ይህንን ትዕዛዝ ይዘው ውርስ አጣሪዎች እነዚህ አካላት ጋር በቀረቡ ጊዜ በራቸው ላይ የሚለጠፍ ማስታወቂያ ከክፈለ ከተማው ያገኛሉ። ይህ ማስታወቂያ የንብረቱ ባለቤት በማረፋቸው ንብረቱ ለወራሾች ሊከፋፈል እንደሆነ እና በዚህ ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ባይ እንዲቀርብ የሚጠይቅ ሲሆን ይህ ማስታወቂያ በዚህ ይዞታ ላይ ለአስር ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ መቆየት አለበት። አስር ቀናቶች ካለፉ በኋላ አጣሪዎች ይህንን እንዳደረጉ ለክፈለ ከተማው አካል ሲያሳውቁ ይህንን የሚገልጽ ለፍርድ ቤቱ የተጻፈ ሰነድ ይቀበላሉ።

፱. አውራሹ ባንክ ውስጥ ገንዘብ ሊኖረው ይችላል። በመስሪያ ቤቱ ብድርና ቁጠባ ወይም በሌሎች ማዕከላት የተቆጠበ ገንዘብ። በተለያዩ ተቋማት ድርሻ ሊኖረው በኩባንያዎችም የአክሲዮኖች ባለቤት ሊሆን ይችላል። ከፍርድ ቤቱ እነዚህ ሀብቶች ምን እንደሆኑ እና የት እንደሚገኙ የያዛቸው ድርጅት እንዲገልጽ ማህተሙ ያረፈበት ደብዳቤ ውርስ አጣሪው ወይም አጣሪዎቹ ማግኘት አለባቸው። ደብዳቤውን መጻፍ የውርስ አጣሪው ድርሻ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ተገቢነቱን መርምሮ ማህተሙን ያሳርፍበታል። ውርስ አጣሪዎቹ እነዚህን ደብዳቤዎች ለተቋማቱ ማድረስ እና የታሸጉ ምላሾቻቸውን መሰብሰብ አለባቸው።

፲. እነዚህን መረጃዎች አሟልቶ ከጨረሰ በኋላ ውርስ አጣሪው ሪፖርት ያዘጋጃል። በዚህ የሪፖርት ሰነድ በውርሱ የሚገኙ ንብረቶች ዝርዝር የሚቀመጥ ሲሆን ውርስ አጣሪው ዋጋቸውን ግምት በዚሁ ሪፖርት ያኖራል። ይህ ዝርዝር እንደተዘጋጀ ውርስ አጣሪው ወራሾችን ማሳወቅ ሲኖርበት ወራሾችም የዚህ ራፖር ግልባጭ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ። በመጨረሻም የተዘጋጀው ይህ ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል። ፍርድ ቤቱም ይህንን ሰነድ ለህጋዊነቱ የሚመረምር ሲሆን ተገቢ ሆኖ ካገኘው ወራሾችን በአንድነት ጠርቶ በጉዳዩ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ይጠይቃቸዋል። በኑዛዜው ላይ ተቃውሞ ወይም አስተያየት ካለ ፍርድ ቤቱ

ሪፖርቱን ማሻሻል፣ ጭብጥ ለይቶ ወራሾችን ማከራከር ወይም ሌላ ሪፖርት እንዲዘጋጅ ማዘዝ ይችላል:: ወራሾች ተቃውሞ ከሌላቸው ግን ፍርድ ቤቱ ሪፖርቱን እና በውስጡ ያለውን የድርሻ

ክፍፍል ስርዓት አጽድቆ ፍርድ ይሰጣል::

፲፩. ወራሾች ይህንን ፍርድ ይዘው የወራሽነት ሰርቲፊኬት እንዲሰጣቸው ፍርድ ቤቱን ማመልከት ይችላሉ:: ይህ ሰርቲፊኬት አንድ ወራሽ ከውርሱ ምን ያህል እንደሚደርሰው የሚያመላክት ይሆናል:: ወራሾች ይህንን ሰርቲፊኬት በመጠቀም ንብረታቸውን በተመለከተ መንቀሳቀስ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ይህንን ድርሻቸውን አስይዘው ብድር መግባት፣ ንብረቶቻቸውን በራሳቸው ስም ማዞር፣ ክፍያ መፈጸም እና የመሳሰሉትን ማድረግ ይችላሉ:: ትችላላችሁ::

የውርስ ንብረትን ለመረከብ እንዴት ንብርቶች እና ድርሻዎች እንደሚለዩ በዚህ ክፍል በሰፊው እንደዳሰስኩላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ:: ግን ወራሽነትን ማጠቃለል በዚህ ስለማይፈጸም በሚቀጥለው ክፍል እንዴት ይህንን ድርሻ መከፋፈል እንደሚቻል እናያለን:: አሁን ያነበባችሁት ግን የወለሉ አናት፣ ወፍ በረር እይታ ነው፤ ህጉ ይህንን በተመለከተ ብዙ ይላልና ህግ ባለሙያዎቻችሁን እያማከራችሁ ጉዳያችሁን ጨርሱ:: እኔም በዚሁ ደመደምኩ:: ሰላም::

ራህዋ ተስፋዬ ቾርነት፤ LL B, LL M, LL M ©2016 የደራሲዋ መብት በህግ የተጠበቀ ነው::

JOIN ABOUT-LAW

Face Book- https://m.facebook.com/aboutlawlegalservice

Telegram- https://telegram.me/ethiolawblog

LinkedIn- https://www.linkedin.com/company/aboutethiopian-law